# ሀገርን እንደ ሀገር ለማዝለቅ

**ዘሪሁን ጎሳዬ**

ዴሞክራሲያዊ አስተዳደርን እንተገብራለን የሚሉ ሀገራት በሙሉ የሥልጣኔ ምንጭ ተደርጎ የሚወሰደው ምርጫ እንደሆነ ሁሉም የሚስማማበት ጉዳይ ነው ብዬ አምናለሁ።

አንዳንድ የሀገራችን የፖለቲካ ፓርቲዎች ጥንካሬያቸውንና ብቃታቸውን ለሕዝብ በማስመስከር የሕዝብን ድምፅ ከምርጫ ኮሮጆ በማግኘት ወደ ሥልጣን መምጣት ሲሳናቸው፣ ሁኔታዎች ጥሩ አጋጣሚ የፈጠሩ በመሰላቸው ጊዜ ሁሉ ለሥልጣን ያበቃናል የሚሉትን ቀዳዳ ለመጠቀም ሲማስኑ ይስተዋላሉ።

እነዚህን ሰዎች የተጠናወታቸው የሥልጣን ሱስ የማይገባንና የማይሆን መንገድን እንዲሞክሩ ቢያደርጋቸውም፣ ሊሳካላቸው እንደማይችልና ከቅዠት የዘለለ የሚፈይደው ነገር እንደሌለ ሊያውቁት ይገባል እላለሁ፡፡

ይህችን ዐረፍተ ነገር በመግቢያዬ ላይ ለማንሳት የወደድኩት የእኛን አገር አንዳንድ የተቀዋሚ ፓርቲ አመራሮች ሰሞኑን በሰሜን አሜሪካ ያካሄዱትን ውይይት እንዲሁም ከአሜሪካ ድምፅ ራዲዮ ጋር ያደረጉትን ቃለ ምልልስ ላይ ያለኝን አስተያየት ለመስጠት ነው።

በህገ መንግሥታችን በግልፅ እንደተደነገገው ብቸኛው የሥልጣን ምንጭ የምርጫ ኮሮጆ እንደሆነ፣ ከዚህ ውጪ ሀገር የማስተዳደር ሥልጣን በነውጥ አሊያም በኩርፊያና ማስፈራራት የሚቸር የፀዲቅ ዳቦ እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል፡፡

አንዳንድ የተቀዋሚ ፓርቲ መሪዎች ሕዝብን እንደማናውቅ፣ እውነታን አመዛዝነን ፍርድ እንደማንሰጥ አድርገው የሚያዩበትን ሁኔታ ሳይና ስሰማ እጅጉን ይገርሙኛል፡፡ ለአብነት ያህል ላንሳ።

ምርጫ 2002 ላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይሆነኛል፣ ይበጀኛል ላለው ፓርቲ ድምፁን ሰጥቶ ሳለ የተለያዩ የተቀዋሚ ፓርቲ መሪዎች ግን ሌላ ሌላ አሉ፡፡ ሕዝቡ ግና ለፈለገው ድምፁን ሰጠ፡፡ የተቀዋሚ ፓርቲ መሪዎች ግን የሕዝቡን ድምጽ ለመረጠው መስጠትን አምኖም ላለመቀበል ሲሉ የተለያዩ ምክንያቶችን ሲደረድሩ ነበር።

ከነዚህም መካከል አንዱ አቶ ገብሩ አሥራት ሲናገሩ "ከእንግዲህ በነበረው እንሂድ ሊባል አይቻልም፣ ምክንያቱም ኢትዮጵያ በከፍተኛ ችግር ላይ ነች የሚል አስተያየት አለን።" ብለው ነበር።

ይህ ማለት ምን ማለት አቶ ገብሩ? እኛ ድምፅ የሰጠነው ይሰራልናል ብለን ላመንበት ፓርቲ ነው። የሀገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር በመሞታቸው ምክንያት የኢህአዴግ መዳከም ይደርስበታል፣ ስለዚህ ይህን መልካም

አጋጣሚ በመጠቀም ኢህአዴግን በማስገደድ ወደ ድርድር እናመጣዋላን ተብሎ ታስቦ ከሆነ እንደ እኔ እንደ እኔ መልካም ነገር አይመስለኝም።

በእርግጥ ድርድር መልካም ቢሆንም እንዲህ ባለበት ሁኔታ፣ ማለትም የመሪን ሞት ምክንያት በማድረግ ድርጅቱን አስገድዶ ወደ ድርድር ማምጣት ይቻላል ብዬ ግን አላምንም።

ባለፈው ምርጫ ድምፃችንን ለኢህአዴግ የሰጠነው በወቅቱ ይዞ በቀረበው የልማትና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች እንደሆን መታወቅ አለበት።

ይህ ፖሊሲና ስትራቴጂም ሊካድ የማይቻል ተጨባጭ ለውጥ በሀገራችን ላይ ማምጣት ችሏል። ታዲያ ይህ ሆኖ ሳል ኢህአዴግ የወሰደውን ኮንትራት ሳያበቃ

በጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ሞት ሲከተለውና ሲተገብረው የነበረው ፖሊሲ የሚለውጥበት ምክንያት ይኖራል ብዬ አላምንም።

አቶ አሥራት "አሁን ሀገራችን በከፍተኛ ችግር ላይ ነች ይላሉ" ይህ አባባላቸው ለእኔ ግልፅ አይደለም። አቶ መለስ ሞቱ እንጂ ኢህአዴግ እንዳለ መሆኑን የተገነዘቡት አይመስለኝም።

አንዳንድ የተቀዋሚ ፓርቲ አመራሮች እንወክለዋለን የምትሉትን የሕዝብ ክፍል በቅጡ ያምታውቁት አይመስለኝም። በእርግጥ እናንተ የሕዝቡን ፍላጎት መረዳት ቢያቅታችሁም ሕዝቡ እናንተን አብጠርጥሮ እንደተረዳናችሁ ልትገነዘቡት ይገባል።

የሕዝብ ፍቅር፣ የሕዝብ አደራ፣ የሕዝብ ጥቅም፣ የሕዝብ አለኝታነት፣ የሕዝብ ወገንተኝነት፣ የሕዝብ አጋርነት እንደ ሻማ ነዶ ማለቅ እንደሆነ ታላቁ መሪያችን አሳይቶናል፡፡ ይህን እናንተ ጎራ አለ ብዬ ለመቀበል ይቸግረኛል።

ምክንያቱም የሀገራችን ተቃዋሚ ኃይሎች እጅግ በጣም የተበጣጠሳችሁ፣ እርስ በእርስ የማትተማመኑ፣ በአጭር ጊዜ ተሰባስባችሁ ደግሞም በማምንታችሁ መበታተናችሁ፣ የፖለቲካ ሥልጣን የጥቅም ምንጭ አድርጋችሁ መቁጠራችሁ (ሁላችሁንም ማለቴ አይደለም)፣ የተቃዋሚው ፓርቲ አመራር መሆንን እንደ ዝና የምትቆጥሩ፣ በየአደባባዩ እርስ በእርስ የምትዘላለፉና አለፍ ሲልም በቆመጥ ስትናረቱ የምትታዩ፣ በተናገራችሁበት የማትፀኑ መሆናችሁ የአደባባይ ሚስጥር ነውና፡፡ ይህ የሥነ ምግባር ጉድለታችሁ ስብዕናችሁን ክከፉኛ የሸረሸረው በመሆኑ ሕዝቡ በእናንተ ላይ አመኔታ እንዲያጣ አድርጎታል።

እናንተም ይህን ከጋራ የገዘፈ ችግራችሁን በመገንዘባችሁ ይመስለኛል ሥልጣንን ከምርጫ ከኮሮጆ ከመጠበቅ ይልቅ አቋራጭ መንገዶችን ማማተርን ሥራዬ ብላችሁ የተያያዛችሁት፡፡

ሀገራችን መድብለ ፓርቲ ሥርዓትን መተግበር ከጀመረችበት ጊዜ አንስቶ የተቃዋሚው ጎራ በአቋራጭ የሥልጣን ወንበር መፈናጠጫ ልክፍት እንደተጠናወተው በየጊዜው ከሚያደርጉት ነገሮች መረዳት የሚያስቸግር አይመስለኝም።

ቅንጅት በ97ቱ ምርጫ ባደረበት ከፍተኛ የሥልጣን ጥም ሣቢያ ያላሸነፈበትንና ያልተገባውን ወንበር ሲፈልግ ያሸነፈበትንና ሕዝብ አደራ የሰጠውን ጭምር እንዳይሆን ... እንዳይሆን አድርጎ ሀገሪቱን ወደ ብጥብጥ እንድትወርድ አደረጋት፡፡

በሀገራችን እየዳበረ የመጣውን የመወዳደር ስሜትና የሕዝብን አማራጭ የማግኘት ፍላጎት በቅንጅት የማይገባ አካሄድ አበለሻሸው፡፡ ከባዱና ጊዜ የሚፈልገው ነገር ነገሮችን ማስተካከል ብሎም መልክ መልክ ማስያዝ እንጂ መናድና ማወሳሰብ ቀላል እንደሆነ የተረዳሁት በ97ቱ የቅንጅት አካሄድ ነው፡፡

በእርግጥ ሥልጣንን ከኮሮጆ የሚጠብቅ የፖለቲካ ፓርቲ የጠራና አማርጭ ሊሆን የሚችል ፖሊሲና ስትራቴጂ መንደፍ የሚችል እንዲሁም ይህን ፖሊሲና ስትራቴጂ ሊተገብር የሚችል በመልካም ስብዕና የታነፀ አመራር ሲኖረው ነው።

የሀገራችን ተቀዋሚዎቸ እንዲህ ያለ እውቀትና ችሎታ ስለሌላቸው ዓይናቸውን በጨው አጥበው አማራጭ ታይቶናል፤ ይህ እድል እንዳያልፈን በሚሉበት ጊዜ የማይገባቸውን መንገድ መከተላቸው የማይቀር ነው ብዬ አምናለሁ። ባይሳካም።

ዛሬ ለሕዝባችን የቁራ ጩኸት ምንም ሲፈይድለት አላየንም፡፡ ሁሌም ችግሮችን ከመንቀስ የመፍቱ አካል የመሆንና ወደ ውስጥ መመልከትንም ልመዱ። መፍትሄ በጋራ እንፈልግ።

ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማሪያም የሥልጣን ጥማቱን ለማርካት ሲል ደግሞ ደጋግሞ ለሕዝብና ለሀገር እንደሚሰራ እስከሚሰለቸን ያላዝንብን ነበር፡፡ መጨረሻው ምን እንደሆነ ለእናንተ አልነግራችሁም፡፡

ሌላው የተቃዋሚ መሪ አቶ ተመስገን ዘውዴ እንዲህ ብለዋል፡፡ "የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጭቆና ወደ ጭቆና እየተሸጋገረ ሊሆን ይችላል። በአቶ መለስ አስተዳደር የዴሞክራሲ ሥርዓት የታፈነበት፣ የመድበለ ፓርቲ ሥርዓት የታፈነበት፣ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አባሎቻችን ከፍተኛ ዋጋ የከፈሉበት ሥርዓት ነበር" ይላሉ።

አቶ ተመስገን እንዲህ መናገር የቻሉበትን ሥርዓት ዋጋ ማሳጣት ተገቢ አይመስለኝም። በሀገራችን ስላለው መድብለ ፓርቲ ሥርዓት፣ ታፈን ስላሉት ሁኔታ ትክክል አይመስለኝም።

ምክንያቱም በምርጫ 2002 የተለያዩ ፓርቲዎች ተወዳድረው ድምፅ ያገኘው ፓርቲ መንግሥት መሰረተ። እርስዎንና ባልደረቦችዎን ከፓርላማ ጠራርጎ ያስወጣችሁ የሕዝብ ድምፅ እንጂ ኢህአዴግ እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል።

አቶ ተመስገን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጭቆና ወደ ጭቆና እየተሸጋገረ ነው ላሉት ነገር ሕዝቡ ከጭቆና እንድንላቀቅ ከፈለጋችሁ የተሻለ አማራጭ ይዛችሁልን ቅረቡ። ካልሆነ ግን አሁን ባላችሁ ስብዕና እናንተ ጨቋኝ የምትሉት ኢህአዴግ በጣም … በጣም እንደሚበጀን እንዲያውቁት እንፈልጋለን።

አቶ ተመስገን ያክሉናም በአቶ መለስ ሥርዓት አባሎቻችን ከፍተኛ ዋጋ የከፈሉበት ጊዜ ነበር ይሉናል። አቶ ተመስገን ይህቺ ሀገር በህግና ሥርዓት የምትመራ መሆኗን የዘነጉት ይመስለኛል። ምክንያቱም ማንም ሊያስጠይቀው

የሚችልን ተግባር ከፈፀመ የየትኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባል ቢሆን ከህግ በላይ ሊሆን እንደማይችል ሊታወቅ ይገባል።

ኢህአዴግ በራሱ ነባር አባላት ላይ ሳይቀር የህግ የበላይነትን ተፈፃሚ እንዳደረገ ሁሉ አሁን ደግሞ በእናንተ አመራሮች ላይ ተግባራዊ ማድረጉ ሊያስመሰግነው እንጂ ሊያስወቅስ የሚገባ ተግባር አይመስለኝም።

አቶ ሥዬ አብርሃ ደግሞ በበኩላቸው "እውነቱን እንናገር ከተባለ አቶ መለስ ህግ ነው፣ ፍርድ ቤትም፣ የመንግሥት ዋና አስፈፃሚውም ነው። እርሱ ያለው ነገር ህግ ሆኖ ይወጣል፤ ነፃ ፍርድ ቤት የሚባል የለም - እርሱ ያለው ፍርድ ሆኖ ይወጣል። ስለዚህ የኢትዮጵያ መንግሥት ተቋማዊ አሰራር የለውም። ነፃ የዳኝነት ሥራ የለም፣ ነፃ የህግ አውጪ የለም፣ የህግ የበላይነት የለም።" ነበር ያሉት፡፡

አቶ ሥዬ እርስዎ እየነገሩን ያለውን ነገር ሌላ ተናግሮት ቢሆን ኖሮ ይሻል ነበር። ምክንያቱም አቶ ሥዬ በኢህአዴግ ከፍተኛ አመራር ሆነው ቢያንስ ከአሥር ዓመታት በላይ ሲያገለግሉ እንደነበር የሚታወስ ነው። አቶ መለስ ራሳቸው ህግ ከሆኑ ይህን ያህል ዓመት እንዴት ለአንድ ዓላማ ተስማምቶ መስራት ይቻላል። ይህ አባባልዎ የሚያስተዛዝብ አይመስልዎትም?

እንግዲህ አቶ ሥዬና አጋሮችዎ ይህን ዓይነት አካሄድን መከተልን የመረጣችሁት እውነት ለሀገርና ለሕዝብ በማሰብ ነው ወይስ በገኛችሁ ፓርቲ ክፍተት የተፈጠረ ስለመሰላችሁ፣ ያቺን ቀዳዳ በመጠቀም ወደቋመጣችሁላት ሥልጣን ታሸጋግረናለች ብላችሁ አስባችሁ ይሆን?

በእርግጥ መልሳችሁ ምን እንደሆነ ባላውቅም የምገምተው ነገር አለኝ፡፡ ይህ አካሄዳችሁ ብዙ ርቀት የሚያስኬዳችሁ አይመስለኝም። የተሻለው አማራጭ ራስን ለአማራጭነት ማዘጋጀት ይመስለኛል። ዛሬ በተቃዋሚ ፓርቲዎች ዙሪያ በቡድንም

ይሁን በግለሰብ የተሰባሰቡትን ስንመለከት በአንድም ይሁን በሌላ ከገዥው ፓርቲ በሥነ ምግባር የተባረሩ፣ አሊያም ከሌሎች ተወዳድረው ማሸነፍ የማይችሉ ደካሞች፣ በሥራቸው እውቅና ማግኘት ሲሳናቸው በአቋራጭ አትኩሮት ለመሳብ ከተናገሩ በኋላ የሚያስቡ፣ ሊተገበር አይደለም ሊታሰብ የማይቻልን ነገር ከተመረጥን እንተገብራለን እያሉ በምርጫ ሰሞን በየአደባባዩ የሚደሰኩሩ፣ የበሬ ወለደን የፈጠራ ወሬ የሚያራግቡ በመሆናቸው በሕዝብ የተናቁና የተጠሉ ናቸው፡፡

በዚህ ተግባራቸው ከሕዝቡ የራቁትና በነፃ ውድድር ማሸነፍ የተሳናቸው አንዳንድ  የሀገራችን ተቃዋሚዎች የመና አውርድ ፀሎታቸው የሰመረ በመሰላቸው ጊዜ ሁሉ አዲስ የሥልጣን ኮርቻ መፈናጠጫ መንገድን ከመማተር አልተቆጠቡም፡፡

የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ሞት እናንተ እንደምትሉት ባይሆንም ኢህአዴግንና ሀገራችንን ብሎም አፍሪካን እንደሚያጎድላት ምንም የሚያጠራጥር ባይሆንም፣ መታሰብ ያለበት ግን አቶ መለስ ራሳቸው የኢህአዴግ ውጤት መሆናቸውን መዘንጋት የለበትም።

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ በድርጅቱ ውስጥ ጉልህ ሚና እንደነበራቸው ሊስተባበል የሚቻል ሀቅ ያለመሆኑን የአፍሪካና የዓለም መሪዎች በአደባባይ የመሰከሩት እውነታ ነው።

ነገር ግን ኢህአዴግ ሌሎች ብቃት ያላቸው አመራሮችም እንዳሉት አፍ ሞልቶ በአደባባይ መናገር ይቻላል። ግለሰቦች በየትኛውም ጊዜና ቦታ በድርጅት ውስጥ ገነው ይወጣሉ፡፡ ነገር ግን እንደ ኢህአዴግ ያለ አንጋፋ ድርጅት በአንድ ሰው ስብዕና ላይ ብቻ ተንጠልጥሎ የኖረ እንደሆነ የሚነገረው ውኃ የሚቋጥር ጉዳይ ሊሆን አይችልም።

ኢህአዴግ የሕዝብን አመኔታና ከበሬታ ያገኘው እንደ ሻማ ቀልጠው በጠፉት ቆራጥ የድርጅቱ አመራሮች ቀንና ማታ፤ በገጠርና ከተማ ያለመታከት በመስራት እንጂ በምርጫ ሰሞን በመሰባሰብ የማይጨበጥ ተስፋ እየነዙ ወይም የአውሮፓና አሜሪካ ሀገራትን መንግሥታት ደጅ እየጠኑና እጅ እየነሱ እንዳልሆነ ማንም ቅን ልቦና ያለው ሁሉ ሊመሰክረው የሚችል እውነታ ነው፡፡

እውነተኛን የሕዝብ አደራን አንግበው የተነሱት የሕዝብ ልጆች የተጣለባቸውን አደራ ለመወጣት ሲሉ እንደሻማ ቀልጠው ለዘለዓለም የሚታሰቡበትን ሀውልት በእያንዳንዱ ኢትዮጵያውያን ልብ ውስጥ ተክለው አልፈዋል፡፡ ሁላችንም ከዚህ መልካም ተግባር ልንማር ይገባል፡፡

አንዳንድ የእኛ ሀገር ተቃዋሚ አመራሮች የሕዝብን አመኔታ የሸረሸረባቸውን ነገሮች ነቅሰው አውጥተው የመፍትሄ አቅጣጫ ከማስቀመጥ ይልቅ ወደ ሥልጣን መሰላሉ ያደርሰናል የሚሉትን ማንኛቸውንም መንገድ ከመሞከር ወደ ኋላ እንደማይሉ ማየት ይቻላል፡፡

በነፃው የትግል ቦታ ላይ ተወዳድሮ ማሸነፍና ወደ ሥልጣን መምጣት የተሳናቸው እነዚህ ግለሰቦች የማይገባ አካሄድ እየተከተሉ ከሕዝቡ ከመራቃቸው ባሻገር የሀገራችንን የዴሞክራሲ ሥርዓት እንዳያጫጩት ሥጋት

አለኝ። ምክንያቱም በእንዲህ ያለ መንገድ  የሥልጣን ኮርቻውን የተፈናጠጠ ፓርቲ ምን ሊያደርግ እንደሚችል ማሰብ ብዙ የሚከብድ አይደለምና።

ኢህአዴግ እንዲገዝፍና በሕዝብ ዘንድ ተመራጭና ተወዳጅ ፓርቲ እንዲሆን ያደረገው በዋናነት እስካሁን ያከናወናቸው ሥራዎች ቢሆኑም፣ የተቀዋሚዎች መልፈስፈስና በቃላቸው ያለመገኘትም የራሱ የሆነ አስተዋፀኦ ያለው ይመስለኛል።

እርስ በእርሱ በአደባባይ ሲናረት የሚውለውን የተቃዋሚ አመራሮችን ኅብረተሰቡ እየተመለከተ እንዴት አደራ ይሸከማሉ ብሎ አደራ ይስጣቸው። በ1997ቱ ምርጫ ወቅት ኢህአዴግ በአዲስ አበባ ተገቢውን የልማት ሥራ ባለማከናወኑ ኅብረተሰቡ አማራጭ ላለው ድምፁን መስጠቱ ይታወሳል።

ይሁንና ቅንጅቶች ያገኙትን እድል ሲያበላሹት ኢህአዴግ ከምርጫ በኋላ ድክመቱን ነቅሶ በማውጣትና ክፍተቱን በማረም ለቀጣዩ ምርጫ ጠንክሮ በመስራት የሕዝቡን ቀልብ ብቻ ሳይሆን የተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላትን ጭምር ለመሳብ በመቻሉ በ2002ቱ ምርጫ ውጤቱ የተገላቢጦሽ ሊሆን ችሏል፡፡

አሁንም ለሀገሬ የተቃዋሚ ጎራ አመራሮች ጆባ የምላችሁ ምክር ምርጫ የአምስት ዓመት ዑደት ነው፡፡ ሥልጣን የዘላለም ወንበር አይደለም፣ በሥልጣን ላይ ሊቆይ የሚቻለው የሕዝብን አመኔታ ማትረፍ እስከተቻለ ድረስ የኮንትራት ውሉ ሊራዘም የሚቻልበት ሁኔታ ይኖራል፣ ይህ ካልሆነ ግን የሕዝብ አመኔታ ሊገኝ አይቻልም፡፡

ኢህአዴግ እንዲህ ያለ የሕዝብ አመኔታን ሊያተርፍ የቻለው በውጭ መንግሥታት ተፅዕኖ አሊያም በፆም በፀሎት እንዳልሆነ ሊዘነጉት አይገባም፡፡

አሁን ... አሁን የምናያቸው ፖለቲከኞች ነን ባዮች "የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው" ዓይነት ትርፍን እንጂ ሌሎች ተያያዥ ሁኔታዎችን ታሳቢ የማያደርግ አካሄድ የሚከተሉ ይመስለኛል፡፡

ከዚህ የሚያገኙት ትርፍ ደግሞ ሀገርንና ሕዝብን ታሳቢ ያላደረገ፣ ውጤቱ ለትውልድ የሚተርፍ ነቀርሣን ትቶ ማለፍ እንደሚሆን ሊዘነጋ የሚገባ አይመስለኝም፡፡

ሀገር ያለ እውቀት አይመራም፣ ሀገር ያለ መቻቻልና መከባበር ዘላቂነት ሊታሰብ አይቻልም፣ ሁሉንም ያማከለ በተቻለ አቅም የሁሉንም ጥቅም ያስጠበቀ ሥርዓት እስካልተመሰረተ ድረስ ሀገርን በሀገርነቷ ለማዝለቅ ይከብዳል፡፡